# ብአዴን ሆይ!

## ነፍስ ይማር!!!




በአንድ ከይሲ ዘመን መልዓከ-ሞት ነግሶ ምድራችን ሲያርድ፤
የሀገር አድባር ከፍቶ ሀጣንን አንግሶ በፃድቃን ሲፈርድ፤
በጥቁር ሰማይ ስር የደመና ጉድ፤ በአገራችን ጣራ ጣለብን በረድ፤
ምድርም አበቀለች አንዳች አራሙቻ ሰብል የሚያነጉድ፤
በአማረው ስንዴ እራስ አረማሞ ድቃይ የዘር እንክርዳድ፤
**‘ፈርዖን - ብአዴን’ ሕዝቤን ለቀህ ውረድ በውድም በግድ።**

በሰው ፍግ የፋፋ፤ ፃዕዳው የከረፋ 'ብአዴን' ባእድ፤
የ‘ንጉስ’ ጃንደረባ አማራን ከእርስቱ ነቅሎ እሚያሳድድ፤
የጓሯችን ሳማ ለብልቦ እሚ-ያስፈጀን እርመ በላ ግንድ፤
የአማራ ጽንስ ውራጅ ለሸጠው ለገዛው የሚያጎበድድ፤
ለጌታው አጉብጦ እድሜ ልክ የሚድህ ቀንቶ አይራመድ፤
ታቻምና ወያኔ ዘንድሮ ለአነግ ቀፈቱ ተጭኖ ወዶ የሚያረግድ፤
ጀርባ አጥንት የሌለው ለከርሱ የሚኖር ዙሪያ ገባው ሆድ፤
የጠላት አርጬሜ ‘ቼ!’ እሚቀባበሉት መግረፊያ ትውልድ፤
ሕዝብ ቆርጦ ይማግደው ብሶት አቀጣጥሎት ባስነሳው ሰደድ፤
**በራሱ ምድጃ ድሮም አፈር ምሱ ይንከባለልበት አህያው ባመድ።**

ከሃዲ ሰብሰብ እግር ተውርች አስሮን እንዳንራመድ፤
ሰላሳ ዓመት ቆዘምን የራሳችን እዳ ሳይወራረድ፤
በአማራ ኪሳራ አሳር አስከፈሉን አይነትም ወለድ፤
**ካባ እያለበሱ አራጅና አሳራጅ በአማራ ነፈስ ቃብድ።**

አማራን ከሚገድል ብልፅግና ጓዳ ከፋሽስቱ ኦነግ የሚሞዳሞድ፤
እልቂቱ አይጨንቀውም የአማራ ኤሎሄ እጅግም ቢከብድ፤
በወለጋ መሬት ለሰማይ ለምድር የሰው ልጅ አበሳ አስፀያፊ ጉድ፤
ሶስት ሺህ ንፁሀን በአረመኔ ታርደው የደም ጎርፍ ሲወርድ፤
ምድረ ብልግና የስላቃቸው ጥግ በሺህዎች መቃብር ዘንቶ መቀለድ፤
ነቅለው ይተክላሉ በሰው ደም ሊያጸድቁ ምድረ ገነታቸው የችግኝ አፀድ፤
የመደመር ንጉሥ አፈ ጮሌ ካድሬ አማራ ቢቀነስ መች ይለዋል ግድ፤
ማቅ ቢለብስ አማራ ሞቱ ብርቅ አይደለም በፓርላማው ዘንድ፤
እልቂት መርዶ አይሰሙም የተኮባበሩት ጂኒያቸው ሳይፈቅድ፤
**ዋናው አጀንዳቸው በሕግ ማስከበር በታንክ በመትረየስ ፍኖን ማሳጨድ።**

በቃኝ! አለ አማራ በቀይ ደም አሻራ ምጡን ሊገላገል ሊከብድ፤ ሊወልድ፤
ትርፍ አንጀቱን ቆርጦ፤የእንግዴ ልጅ ቀብሮ ዳግም ካፅመ እርስቱ እንዳይሳደድ፤
ቆርጧል በአለም ዙሪያ ትግሉ እንዲቀጣጠል ኃይዎት መድናችን የፋኖ መንገድ፤
አማራ ያበስራል የኢትዮጵያን ትንሳኤ ካህዲዎች ወርደው መቀመቅ ጉድጓድ፤
ከሃውልቱ ግርጌ ስማቹህ ይጻፋል ሥራ ምግባራቹህ አፅም የሚያስርድ፤
'ብአዴን-ብልፅግና' ሳይመሽብህ ውረድ ሌሊቱ ሳይነጋ ሳታረፍድ ውረድ!
ውረድ! ውረድ! ውረድ! ውረድ! ውረድ! ውረድ! ውረድ! ውረድ!
**መታሰቢያነቱ በቁም ለተሰዉት ለብአዴን ሙታን በስም ተዋረድ።**




ከጥላሁን መኮንን
ሰኔ 23፤ 2014